የሲቪል መከላከያ

የትምህርት ሚኒስቴር

# በትምህርታዊ ተቋሞች ውስጥ
# ብሔራዊ የመከላከያ ልምምድ

**መጋቢት 12 ቀን 2019 ዓ.ም. ה' באדר ב' תשע"ט**

## ለወላጆች የተላከ ደብዳቤ

የትምህርት ሚኒስቴርና የሲቪል መከላከያ (“ፒኩድ ሀያሬፍ”) በየዓመቱ በእስራኤል አገር ውስጥ በሚገኙ ሁሉም ትምህርታዊ ተቋሞች ውስጥ የመከላከያ ልምምድ ያካሂዳሉ። የመከላከያ ልምምዱ ትምህርታዊ ተቋሞች ለተለያዩ ድንገተኛና አስቸኳይ ሁኔታዎች ራሳቸውን ዝግጁ እንዲያደርጉ የሚያስችል ወሳኝ ነጥብ ነው።

**ዘንድሮ ልምምዱ ማክሰኞ፣ መጋቢት 12 ቀን 2019 ዓ.ም. ה' באדר ב' תשע"ט ከ10:00 እስከ 12:00 ሰዓት ድረስ ነው።**

የዘንድሮ ልምምድ ተማሪዎች ክፍል ውስጥ እየተማሩ እያለ **የመሬት መንቀጥቀጥን** ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ነው። እንደዚሁም ወደ ሜዲቴራኒያን ባሕር ተጠግተው ላሉ የትምህርት ተቋሞች **የሱናሚ አደጋ** ልምምድን ያካትታትል።

**ባለፉት ቅርብ ጊዜያት በዓለም ዙሪያ የመሬት መንቀጠቀጥና ሱናሚ አደጋ መድረሱን አይተናል እንደዚሁም ሰምተናል። ይህም እኛም ለእነዚህ ዓይነት ክስተቶች ዝግጁ እንድንሆን ያስገድደናል።** የትምህርቱ ሥርዓት ለስምሪትና ለአስቸኳይ ሁኔታዎች የሚያሳየው ከፍተኛ ዝግጁነት ዋነኛ ሚና ይጫወታል። ይህ ዝግጁነት የእስራኤል ኅብረተሰብ ድንገተኛ ሁኔታዎችን በጥንካሬ እንዲቋቋም ከፍተኛ ቦታ አለው።

የልምምዱ ስኬታማነት የተመረኰዘው በልጆቻችሁ ሙሉ ትብብርና በእናንተ ድጋፍ ላይ ነው። ስለሆነም ዝግጅቱ በአስቸኳይ አደጋ ጊዜ ጠቃሚ መሆኑን ልጆቻችሁ ይረዱ ዘንድ ስለልምምዱ ከእነሱ ጋር ተነጋገሩ። ይህ በዚህ እንዳለ ለትንንሽ ልጆች እየተደረገ ያለው ልምምድ እንጂ አደጋ ያለበት አስቸኳይ ሁኔታ አለመሆኑን ማስረዳት ያስፈልጋል።

የአስቸኳይ ሁኔታን በጥሩ ሁኔታ መጋፈጥ መላው ቤተሰብና የትምህርት ተቋሙ በሚያደርጉት ዝግጁነት ላይ የተመረኰዘ ነው። ስለሆነም እናንተ ከልጆቻችሁ ጋር ለእነሱ ወደተዘጋጀው ልዩ የ“ፒኩድ ሀያሬፍ” ድረ ገጽ http://kids.gov.il/oref በመግባት ስለ አስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች እንድትማሩ እንጋብዛችኋለን።

**ዝግጅትና በየጊዜው መለማመድ - በአስቸኳይ ሁኔታ ጊዜ በተገቢው ሁኔታ ለመጋፈጥ ዋነኞቹ ቁልፎች ናቸው!**

**ጥያቄዎች ካሏችሁ**

**ለ“ፒኩድ ሀየሬፍ”** ע"פקר **አመልከቱ።**

www.oref.org.il **ስልክ** 104 በቴክስት ለስልክ ቁጥር 052-9104104

**ትምህርት ሚኒስቴር**

http://cms.education.gov.il/EducationCMS/Units/Bitachon/HomePage.htm

**ስልክ** 02-5602234


| | |
|---|---|
| **ሜጀር ጄኔራል ታሚር የዳዒ** | **አቶ ሽሙኤል አቡአቭ** |
| የሲቪል መከላከያ ዋና አዛዥ | የትምህርት ሚኒስቴር ዋና ሥራ አስኪያጅ |